*Ethiop.j.lang.cult.com.mun.2024, 9(2): 180-203* *Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*Open Access Licensed under Creative Commons:* *ISSN: 2518-2919*
*CC BY-NC-ND 4.0*
DOI: 10.20372/ejlcc.v9i2.1860

**Original Research**

# ተረቶችን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂሎት ለማዳበር ያለው ሚና በደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ የ2016 ዓ.ም የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

**Tsehay Hailemeskel Kassa[1*], Lemma Nigatu[2], Wudu Melese[3]**

[1]Jimma University, Ethiopian Language and Literature (Amharic), Jimma, Ethiopia

[2]Jimma University, Ethiopian Language and Literature (Amharic), Jimma, Ethiopia

[3] Jimma University, Department of Teacher Education and Curriculm, Ethiopia

**Corresponding author: hailemeskeltsehay@gmail.com*

## Abstract

This study investigated the effectiveness of using tales to enhance the writing skills of Grade 5 Amharic first language students. A quasi-experimental design was employed with two groups (experimental and control) of 47 students each, randomly selected from among 246 Grade 5 students attending Karagutu Primary School in Desse City, South Wollo Zone, in 2016 E.C. The experimental group received instruction using tales, while the control group followed conventional teaching methods. Pre- and post-test writing assessments were administered to both groups. The analysis of the pretest results t (92) = 0.400, p< 0.690) showed that there was no significant difference between the experimental and control groups. However, after the intervention, the analysis of the post-test results revealed a significant difference in writing skills between the experimental and control groups t (92) = 4.686, p< 0.05). These findings suggest that incorporating tales into writing instruction can be a valuable strategy for improving the writing skills of Grade 5 Amharic first language students. Therefore, it would be good for the concerned parties to use the method of teaching writing through stories to improve the writing skills of the students.

**Key words**: tale, teaching writing, writng skill, role

*Ethiop.j.lang.cult.com.mun.2024, 9(2): 180-203* *Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*Open Access Licensed under Creative Commons:* *ISSN: 2518-2919*
*CC BY-NC-ND 4.0* DOI: 10.20372/ejlcc.v9i2.1860

የጥናቱ ዓላማ ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ነበር። ለዚህ የሚረዱ መረጃዎች በቅድመ እና ድኅረ ትምህርት ፈተናዎች ተሰበስበዋል። ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ዘዴን ነው። ጥናቱ የተካሄደው በካራጉቱ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በአምስተኛ ክፍል ይማሩ ከነበሩ 246 ተማሪዎች በተራ እጣ ናሙና የተመረጡ 94 (በሙከራ ቡድን 47 በቁጥጥር ቡድን 47) ተማሪዎችን በማሳተፍ ነው። የቅድመ ትምህርት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ለሙከራ ቡድኑ ተረትን በመጠቀም፣ ለቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው መማሪያ መጽሐፍ በተለመደው መንገድ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ተሰጥቶ በመጨረሻም የድኅረ-ትምህርት መረጃዎች ተሰብስበዋል። የቅድመ ትምህርት ፈተናው የባእድ ናሙና ስሌት t (92) = 0.400,P< 0.690 መሆን በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖቹ የመጻፍ ክሂል መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑን አሳይቷል። በአንጻሩ የድህረ ፈተናው መረጃ የባዕድ ናሙና (Independent Samples T-test) ስሌት t (92) = 4.686፣ P<0.05 (.000) ውጤት በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል የመጻፍ ክሂል ልዩነት መኖሩን አመላክቷል። የጥናቱ ግኝትም ተረትን በመጠቀም መጻፍን ማስተማር ከተለመደው መጻፍን የማስተማሪያ ዘዴ በተሻለ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማሻሻሉን አሳይቷል። ስለሆነም የሚመለከታቸው አካላት የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል ለማጎልበት መጻፍን በተረቶች የማስተማር ዘዴን ቢጠቀሙ መልካም ይሆናል።

*ቁልፍ ቃላት፡- ተረት፣ መጻፍን ማስተማር፣ የመጻፍ ክሂል፣ ሚና*

**Citation:** Tsehay Hailemesekel, Lemma Nigatu, Wudu Melese. (2024). ተረቶችን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂሎት ለማዳበር ያለው ሚና በደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ የ2016 ዓ.ም የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት. *Ethiopian Journal of Language, Culture and Communication,* *9*(2).180-203. DOI: 10.20372/ejlcc.v9i2.1860

| *Submitted:August 2024* | *Revised: October 2024* | *Acceptted:December 2024* |
|---|---|---|

# የጥናቱ ዳራ

መጻፍ በመማር የሚዳብር እና ተማሪዎች በጽሁፍ ትርጉም ያለው መልእክት ለማስተላለፍ የሚችሉበት ክሂል ነው፡፡ Al-Zoubi (2019)፣ Belloን (1997) እና Frenchን እና Roderን (1992) ጠቅሰው እንደሚገልጹት፣ መጻፍ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ አጫጭር ጽሁፎችን የመጻፍ ችሎታቸውን ሊያበለጽጉና ሊያሳድጉ የሚችሉባቸውን መረዳቶች የሚጠይቅ አፍላቂ ክሂል ነው፡፡ Joanne and Slater(1987) እንደሚገልጹት ሥነ ጽሁፍ ተማሪዎችን፣ ከበርካታ ስነልሳናዊ ጠቀሜታዎች፣ ቅርጾችና የጽህፈት ሥርዓት ስምምነቶች እና ከተለያዩ የጽሁፍ ቋንቋ ባህርያት ጋር ያስተዋውቃቸዋል፡፡ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሥርዓተ ትምህርት (2009) መርሆች መካከል የሥርዓተ ትምህርቱ ይዘት ከተማሪዎች የእለት ተእለት ህይወት ጋር መዛመድ፣ የትምህርቱ ተገቢነት እና እሴት ከእያንዳንዱ ተማሪ እና ከወጣበት ማህበረሰብ ጋር ተስማሚ መሆን እና የተማሪዎች ክህሎቶች ይገኙበታል፡፡ በዚሁ ሥርዓተ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል (2013) ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ ተገልጿል፡፡ በሰነዱ ውስጥ የአምስተኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ተማሪዎች እንዲያዳብሯቸው የሚፈለጉ የመጻፍ ክሂል ብቃቶች፣ ይዘቶች፣ የፍሰት ሰንጠረዦች እና መርሃ ትምህርቶች ተዘርዝረዋል፡፡

የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ Brougton et al. (1980) እንደሚገልጹት በቋንቋ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መርሃ ግብር ሊቀረጽለት ይገባል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት አቅጣጫም ተማሪዎች የቋንቋውን የአጻጻፍ ስርዓት ስምምነት ተከትለው በአእምሯቸው ያለውን ሀሳብ ለአንድ ዓላማ በተገቢው መንገድ መጻፍ እንዲችሉ ማብቃት ነው፡፡

መጻፍን ለማስተማር ከሚመረጡ ይዘቶች ተገቢነት እና አካባቢያዊነት አንጻር ተረቶች አካባቢያዊ እና የእለት ተእለት ቋንቋን የሚጠቀሙ በመሆናቸው ክህሎቱን ለማስተማር ተገቢ ናቸው፡፡ Joanne and Slater (1987) እና Lazar (1993) እንደሚገልጹት፣ ሥነጽሁፍ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማሪያነት ከሚመረጥባቸው ምክንያቶችም መካከል እውነተኛ ማቴሪያልነቱ፣ የአፈ ፈቱን የቋንቋ አጠቃቀም ለማወቅ ማገዙ፣ ባህላዊ እና ቋንቋዊ ብልጽግናው፣ ግላዊ አካታችነቱ እና ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ባህላዊ ዳራ እና የቋንቋ ደረጃ ጋር በተስማሚነት መመረጥ መቻሉ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ሀብታሙ፣ 2018 Weigleን (2002) ጠቅሰው እንደገለጹት በዚህ ዘመን ባለንበት ማሕበረሰብ ውስጥ ጥሩ የመጻፍ ችሎታ እና መጻፍን

የማስተማር ሚና እየጎላ መምጣት በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጎታል፡፡ ትኩረት የመሰጠቱን ያህል ግን የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ከስህተቶች የጸዳ አለመሆኑን የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ Langan (1997) እንደሚገልጹት፣ ተማሪዎች አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ በአብዛኛው ሰዋሰዋዊ፣ ሜካኒካዊ፣ የሥርዓተ ነጥብ እና የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች ጎልተው ይታያሉ፡፡ እነዚህና መሰል ችግሮች ተማሪዎች ሞዴል የቋንቋ መማሪያ ማቴርያሎችን ካለማግኘታቸው የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ጥናት፣ ከአካባቢያዊነታቸው፣ የዕለት ተለት ቋንቋ ከመጠቀማቸው፣ ከባህላዊና ቋንቋዊ ብልጽግናቸው ወዘተ አንጻር ተረቶችን በማስተማሪያ ማቴርያልነት መጠቀም የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር የሚኖራቸውን ሚና ይመረምራል፡፡

ከላይ በዳራው እንደተገለጸው፣ የመጻፍ ክሂል በኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ትኩረት የተሰጠው ቢሆንም፣ ማረው (1996) እና የአምላክ ሥራ (2008) ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በርካታ ስህተቶችን እንደሚፈጽሙ ይገልጻሉ፡፡ ተስፋየ (1981) እና የአምላክሥራ (2008) ለስህተቶቹ መከሰት በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የማስተማር ስልት፣ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ የተማሪዎች ቁጥር ብዛት ከመጠቀሱት መካከል መሆናቸውንም ይገልጻሉ፡፡

በ2014 ዓ.ም በመርሃ ጥበብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለተግባራዊ ልምምድ በቆየሁባቸው ሳምንታት ባካሄድኳቸው ምልከታዎች በBeshir(2023) ፣ በPutri (2019) እና Broughton et al. (1980) ከተገለጹት ችግሮች፡- የፊደል አጣጣል፣ የአረፍተነገር አመሰራረት፣ የአንቀጽ አወቃቀር፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት እና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጊዜያተ ሰወሰው፣ አንድን ጉዳይ ለመጻፍ ተገቢ ስልት ያለመጠቀም፣ ሊገለጽ የተፈለገውን ጉዳይ በቀላሉ እና በሚመች መንገድ ያለመግለጽ ችግሮችን መመልከቴ፣ ከመጻፍ ክሂል አስፈላጊነት አንጻር ጥናት እንዳደርግ አነሳስቶኛል፡፡

ሌላው በNunan (1998)፣ በByren (1988) እና በHasani (2016) መጻፍን አስቸጋሪ በሚያደርጉ ምክንያትነት የተጠቀሱት፣ ሥነ ልቦናዊ፣ ሥነ ልሳናዊ፣ አእምሯዊ እና ሥነ ትምህርታዊ ችግሮችን መፈተሽ፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማጎልበት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የሚኖረውን ሚና መመርመር በምሁራኑ የተጠቀሱትን ችግሮች አማክሎ ለማየት እንደሚያግዘኝ መገንዘቤም ለጥናት አነሳስቶኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ በአንድ በኩል በተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ለምሳሌ የLazar (1993)፣ Mustefa (2016) (Hill, 1986)ን ጠቅሰው እንደገለጹት እና የመንግስት (2008) የጥናት ውጤቶች ሥነጽሑፍን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እንደሚያዳብሩ ቢገልጹም፣ በሌላ በኩል እነ Mckay (1986)፣ Widdowson (1982) እና Topping (1968) ከዚህ የሚቃረን ውጤት ማስመዝገባቸው፣ እንዲሁም አጭር ልቦለድን ወይም ግጥምን ተጠቅሞ መጻፍን በማስተማር ተጠቃሽ የሆኑ የነቢዩ (2005)፣ የግዛቸው (2014)፣ እና የዘመንፈስ (1991) ጥናቶች ቢኖሩም፣ ተረቶችን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር ላይ የተካሄደ ጥናት አለማግኘቴ፣ ሥነ ጽሑፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ በHill (1986) ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ፡- አውድ ከሳችነት፣ ተግባቦት አጎላባችነትና ተነሳሽነት ፈጣሪነት በተረቶች ጎልተው የሚታዩ ሚናዎች እንደሆኑ በመገንዘቤና በአጠቃላይ ተረቶችን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር ላይ ጥናቶች ባለመካሄዳቸውና በሥነ ጽሑፍ መጻፍን በማስተማር ላይ በተካሄዱ ጥናቶችም ክርክሮች በመኖራቸው ይህን ሙከራዊ ጥናት በማካሄድ ክፍተቱን ለመሙላት ተነሳስቻለሁ፡፡

በጥናቱም የአምስተኛ ክፍል አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን በመማር ረገድ የሚከተለው መላምት ተፈትሿል፤ እሱም፡-

Hypothesis: ተረቶችን በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ያዳብራል፡፡ የሚል ሲሆን በጥናቱ የተነሳው ጥያቄም ተረትን በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ያዳብራል? ነው፡፡

## ክለሳ ድርሳናት

### ቋንቋን የማስተማር ንድፈ ሐሳብ

ቋንቋን በውጤታማ ንድፈ ሐሳቦች፣ አቅጣጫዎችና ዘዴዎች ማስተማር የዚህ ዘመን የመማር ማስተማር መስክ መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን Dos Santos (2020) ይገልጻሉ፡፡ በቋንቋ መማሪ ክፍሎች ሁኔታዎችን መሰረት ያደረገ በጣም ተገቢና ውጤታማ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎችንና ስልቶችን መለየት የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡ ባለፉት ዘመናት የጊዜውን የመማር ፍላጎት ለማሳካት በርካታ ንድፈ ሐሳቦች ቢዳብሩም በባህላዊና ማኅበራዊ ፈጣን ለውጦች ምክንያት በዚህ ዘመን በርካታ ንድፈ ሐሳቦች በልጽገው በተለያዩ አንጻሮችና አተገባበሮች አገልግሎት ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡

በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ከመነሻው በኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ከመወሰን አልፎ የቅኝ ገዥ ሀገራትን ቋንቋዎች ለማስፋፋት ሰዎች በቋንቋዎቹ የበለጠ እንዲግባቡና ማንበብ እንዲችሉ በሥነጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን የማስተማር ዘዴ በስፋት መተግበር እንደጀመረ Hall (2005) ይገልጻሉ፡፡ የሥነ-ጽሁፍ ይዘቶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም አዲስና ቀልጣፋ ዘዴ ተደርጎ በመወሰዱ 1950ዎቹ ጀምሮ መምህራን ዘዴውን በስፋት መጠቀም መጀመራቸውንና ይህ ሂደትም ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን ማስገኘቱን ያስረዳሉ፡፡ ቋንቋን ማስተማር በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተከታታይ ለውጦችና አዳዲስ ግኝቶችና አንዳንዴም በተፎካካሪ የማስተማር ርእዮተ ዓለሞች ባህሪው እንደሚገለጽ Richards (2001) ይገልጻሉ፡፡

እኒህ ተመራማሪ አክለው እንደሚገልጹትም የአሁኑን የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎችና አንጻሮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የቋንቋን ንደፈ ሐሳባዊ እይታዎችና የቋንቋን የችሎታ ባህሪ የሚያሳዩ ቢያንስ ሦስት የተለያዩ ንድፈ ሐሳባዊ መኖራቸውን ይገልጻሉ፡፡ ከሦስቱ በጣም ቆየት ያለው መዋቅራዊ እይታ (structural view) ሲሆን ሁለተኛው ተግባራዊ እይታ (functional view) እና ሦስተኛው ግንኙነታዊ እይታ (interactional view) ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሐሳባዊ እይታ ቋንቋን የሰዎችን የእርስበርሳዊ ግንኙነት እውን ማድረጊያና በግለሰቦች መካከል ማኅበራዊ ግንኙነትን ማሳለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡ ይህ እይታ ወደ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ይመራል፡፡

ቋንቋን የመማር ንድፈ ሀሳቦችን በተመለከተ Richards (2001) እንደሚገልጹት መሰረታዊ የቋንቋ መማር ንደፈ ሐሰቦች በተግባቦታዊ የቋንቋ መማር ውስጥ ይለያሉ፡፡ እነሱም፡- የተግባቦት መርህ (communication principle)፣ የተግባር መርህ (task principle)፣ ሦስተኛው የትርጉም ሰጭነት መርህ (meaningfulness principle) ናቸው፡፡ በተግባቦት መርህ እውነተኛ ተግባቦትን መሰረት ያደረጉ ክንውኖች መማርን ማፋጠናቸውን ያሳያል፡፡ የተግባር መርህ ትርጉም ያለው ተግባርን ለማከናወን የዋለ የቋንቋ ትምህርትን ከማፋጠን ጋር ይገናኛል፡፡ የትርጉም ሰጭነት መርህ ለተማሪው ትርጉም ሰጭ የሆነ ቋንቋ የመማር ሂደቱን እንደሚደግፍ ያሳያል፡፡

በሥነ ጽሑፍ (ተረት) ቋንቋን ማስተማር፣ ተግባቦትን መሰረት ያደረጉ ክንውኖችን፣ ተማሪዎቹን ከባህላቸውና ቋንቋቸው ጋር በተጨባጭ ተግባር የሚያገናኙ ክንውኖችንና ትርጉም ሰጭ የሆነ የመማር ሂደትን ስለሚፈጥር፣ መረጃዎቹን ለመተንተን ንደፈ ሐሳቡ ተመርጧል፡፡ Dos Santos (2020) እንደሚገልጹት በአሁኑ ጊዜ በቋንቋ ማስተማር ሙያ

በጣሚ ጠቃሚ ከሆኑት ተተግባሪ የቋንቋ መማር ማስተማር ንደፈ ሀሳቦች አንዱ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማተማር ዘዴ ነው፡፡

## የመጻፍ ክሂል

መጻፍ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ አጫጭር ጽሁፎችን የመጻፍ ችሎታቸውን ሊያበለጽጉ እና ሊያሳድጉ የሚገባቸውን መረዳት የሚጠይቅ አፍላቂ ክሂል መሆኑን Al-Zoubi (2019)፣ Belloን (1997) እና French and Roderን (1992) ጠቅሰው ይገልጻሉ፡፡ ሥነጽሁፍን በመጠቀም መጻፍን መማር ተማሪዎች ንኡሳን የመጻፍ ክሂሎችን ፣ ተግባቦታዊ ቋንቋ አጠቃቀምን፣ተገቢ ቃላትን እና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን አመራረጥን እና ተገቢ የመጻፍ ስርዓት አጠቃቀማቸውን እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል፡፡ Joanne and Slater (1987) እንደሚገልጹት ሥነጽሁፍ ተማሪዎችን ከበርካታ ስነልሳናዊ ጠቀሜታዎች (ከሥነልሳናዊ አጠቃቀሞች፣ ቅርጾች እና የጽህፈት ሥርዓት ስምምነቶች ፣ከተለያዩ የጽሁፍ ቋንቋ ባህሪያት) ጋር ያስተዋውቃቸዋል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሥርዓተትምህርት (2009) መርሆች መካከል የተማሪዎችን የመማር ክሂሎት ማበልጸግ፣ንቁ ተሳትፎ፣ የትምህርቱ ተገቢነት እና እሴት ከእያንዳንዱ ተማሪ እና ከወጣበት ማህበረሰብ ጋር ተስማሚ መሆን እና የተማሪዎች ከፍተኛ ክሂሎች ይገኙበታል፡፡

የቋንቋ ትምህርት በሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ ሊሰጥ ይገባል፡፡ Brougton et al. (1980) እንደሚገልጹት የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ በቋንቋ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መርሃ ግብር ሊቀረጽለት ይገባል፡፡ በመርሃ ግብሩ ተማሪዎች በትምህርቱ ማብቂያ ሊካኑ የሚገባቸው ዋና ዋና የመጻፍ አይነቶች እና ብቃቶች ይዘረዘራሉ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት አቅጣጫም ተማሪዎች የቋንቋውን የአጻጻፍ ስርዓት ስምምነት ተከትለው በአእምሯቸው ያለውን ሀሳብ ለአንድ አላማ በተገቢው መንገድ መጻፍ እንዲችሉ ማብቃት ነው፡፡ መጻፍን ለማስተማር ከሚመረጡ ይዘቶች ተገቢነት እና አካባቢያዊነት አንጻር ተረቶች አካባቢያዊ እና የእለት ተእለት ቋንቋን የሚጠቀሙ በመሆናቸው ክህሎቱን ለማስተማር ተገቢ ናቸው፡፡ Fakhrutdinova et al. (2019) እንደሚገልጹት ተረቶች ከህዝብ የፈለቁ ስለሆኑ የቋንቋው ተማሪዎች ወጣቶች (ህጻናት) በተረት አማካይነት ተጨባጭ(እውነተኛ) ቃላትን (Authentic Vocabulary) ለመማር ይጋለጣሉ፡፡

ሥነጽሁፍ ቋንቋን ለማስተማር ተመራጭ የሚሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ Joanne and Slater (1987) እና Lazar (1993) እንደሚገልጹት ሥነጽሁፍ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማሪያነት የሚመረጥባቸው የተለያዩ ምክንያቶች፡- የተለየ እና ያልተለመደ ቋንቋ

አጠቃቀሙ ፣ እውነተኛ ማቴሪያልነቱ፣የአፈ ፈቱን ቋንቋ አጠቃቀም ለማወቅ ማገዙ፣ባህላዊ እና ቋንቋዊ ብልጽግናው፣ ግላዊ አካታችነቱ እና ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ስሜት፣ ባህላዊ ዳራ እና የቋንቋ ደረጃ ጋር በተስማሚነት መመረጥ መቻሉ ተጠቃሽ ናቸው። ከላይ በተነሱት የመስኩ ምሁራን ሀሳቦች መሰረት ተረት በቃላዊ ስነጽሑፍ ዘርፍነቱ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ስለሚጋራቸው የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር መዋል ይጠቅማል። ሀብታሙ ፣ 2018 Weigleን (2002) ጠቅሰው እንደገለጹት በዚህ ዘመን ባለንበት ማሕበረሰብ ውስጥ ጥሩ የመጻፍ ችሎታ እና መጻፍን የማስተማር ሚና እየጎላ መምጣት በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጎታል። Langan (1997) እንደሚገልጹት ተማሪዎች አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ በአብዛኛው የሚታዩት ስህተቶች ሰዋሰዋዊ፣ ሜካኒካዊ፣ የሥርዓተነጥብ እና የቃላት አጠቃቀም ናቸው። Byren (1988) መጻፍን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምክንያቶች ሥነልቦናዊ ችግሮች (Psychological Problems)፣ ሥነልሳናዊ ችግሮች (Linguistics problems) እና አእምሯዊ (Cognitive problems) በማለት ሲመድቧቸው Nunan (1998) ሥነ ትምህርታዊ ችግሮችን (Pedagogical problems) በአራተኛነት እንደመደቧቸው Hasani (2016) ይጠቅሳሉ።

መምህራን መጻፍን ሲያስተምሩ መከወን የሚገባቸው ተግባራት አሉ። Broughton et al. (1980) እና Maxom (2009) እንደሚገልጹት መምህራን መጻፍን በማስተማር እና በመማር ሂደት ተማሪዎች በተገቢው እና በስኬታማ መንገዶች እንዲጽፉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ለማሳካት በስነጽሁፍ አማካይነት ለቋንቋ ክሂሎች ማስተማሪያነት የሚጠቅሙ ማቴሪያሎችን መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል። Lazar (1993)፣Joanne and Slater (1987) ሥነጽሁፍ ከቋንቋው ሥነልሳናዊ አጠቃቀም ቅርጾች እና የጽሕፈት ስምምነቶች ጋር የሚያስተዋውቅ፣ ቋንቋዊ ብልጽግና ያለው ፣ ተማሪዎች በእለት ተእለት የሚጠቀሙበት በመሆኑ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ማዋል ጠቀሚ መሆኑን ይጠቁማሉ።

በውጪ አገር ከተጠኑ ጥናቶች ጥናቶች መካከል የBagus (2019) "Promoting Students Writing Skill through Folktale Based Learning Activities." የጥናታቸው ዓላማ ተረቶችን መሰረት ባደረጉ የመማር ተግባራት አማካይነት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማሻሻል ነው። Putri (2019) Using Folktales toTeach Writing Skill at 8th Grade Students. በሚለው ጥናታቸው መረጃ የተሰበሰበው በቅድመ እና ድህረ ፈተና ሲሆን በድህረ ፈተና ተረቶችን በመጠቀም መጻፍን የተማሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች

ውጤት የተሻለ ልዩነት አሳይቷል፡፡ የNur(2017) እና የBagus (2019) ጥናቶችም ተረቶችን በመጠቀም ማስተማር በተማሪዎች የመጻፍ ክህሎት መሻሻል ወይም አለመሻሻል ላይ ያለውን ሚና በመመርመር የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ መሻሻሉን አሳይተዋል፡፡

Nur (2017) ፣Yaakob(2015) እነ Grab and Kaplanን (1996) እና Nunanን (1989) ጠቅሰው እንደሚገልጹት ምናልባት ግማሽ ያህሉ የዓለም ሕዝብ እንዴት ብቁ እና ውጤታማ ሆኖ መጻፍ እንደሚቻል አያውቅም፡፡ መጻፍ እና መጻፍን መማር ከቋንቋ ክሂሎች መካከል አንደኛው ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ Bagous (2019) እነ Oshima and Hogueን (2007) በመጥቀስ እንደሚገልጹት የክሂሉ ጠቀሜታ የጎላ ቢሆንም ተፈጥሯዊ ስጦታ ባለመሆኑ ክሒሉን ለመማር የተወሰነ ጠንካራ ስራ እና ተከታታይ ልምምድ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እነ Rietdijk et al.(2018) እንደገለጹት በርካታ ህጻናት እንዴት መጻፍ እንደሚችሉ ለመማር ይቸገራሉ፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመጻፍ ክሂል ውስብስብ እና በተደጋጋሚ ልምምድ የሚዳብር ችሎታ ነው፡፡ መጻፍ ሀሳብን ማፍለቅ ብቻ ሳይሆን ጥሩ እና ተነባቢ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ጥሩ ጽሁፍ የይዘት ፣የቃላት ምርጫ፣የማደራጀት፣ የሥርዓተ ነጥብ ችግሮች የሌሉበት ነው፡፡ ተማሪዎች እዚህ የመጻፍ ደረጃ ላይ ለመድረስ በሚጽፉበት ጊዜ የሚያደናቅፏቸውን ችግሮች በመገንዘብ ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## መጻፍን በተረት የማስተማር ጠቀሜታዎች

የቋንቋ መምህራን ሥነጽሁፍን (ተረት) በክፍል ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚጠቀሙባቸው ምክንያቶችም የተለያዩ ናቸው፡፡ Lazar (1993) እና Joanne and Slater (1987) እንደሚገልጹት፣ አነሳሽነታቸው፣ እውነተኛ ማቴሪያልነታቸው፣ ቋንቋን ለመልመድ ማነቃቃታቸው፣ የተማሪዎችን የመተረጎም (የመግለጽ) ችሎታ ማሻሻላቸው፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ግንዛቤ ማስፋፋታቸው፣ ከበርካታ ሥነልሳናዊ አጠቃቀሞች ቅርጾች እና የጽህፈት ሥርዓት ስምምነቶች ጋር ለምሳሌ ከውስጠ ወይራ፣ ገለጻ፣ አከራካሪ፣ ተራኪ፣ ጽሁፎች ጋር ማስተዋወቃቸው እና ቋንቋዊ ብልጽግናቸው ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው፡፡ ተረቶች ለተማሪዎች ያላቸውን ጠቀሜታ Fakhrutdinova (2009) እንደሚገልጹት ተረቶች ከህዝብ የፈለቁ ስለሆኑ የቋንቋው ተማሪዎች ወጣቶች (ህጻናት) በተረት አማካይነት ተጨባጭ ቃላትን (Authentic Vocabulary) ለመማር ይጋለጣሉ፡፡ Prastiwi (2015)፣ Bunanta (1998)ን እና Jhonson and Lowis,(1985)ን ጠቅሰው እንደገለጹት

ተረቶች እንደ ታሪክ መግቢያ፣ዋና አካል እና መጨረሻ ስላላቸው ተማሪዎች የታሪክ መዋቅርን በመማር ለመጻፍ ተግባር እንዲያውሉት ይረዳቸዋል፡፡

ተረቶች በማንኛውም ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ጠቃሚ ናቸው፡፡Lwin (2009) Maybin and Parceን (2006) ፣Taylor (2000) እና Bean (1999) ጠቅሰው ተረቶች ቋንቋን ለማስተማር ያላቸውን ጠቀሜታ እንደገለጹት ተረቶች ከቋንቋ ደረጃቸው አንጻር ሲገለጹ በማንኛውም የእድሜ ደረጃ ለሚገኙ የቋንቋ ተማሪዎች ተስማሚ ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ተረቶች አውዳዊ እና ከአውድ ውጪ ትርጉም በመስጠት፣ በመተንተን፣ በማጠቃለል እና የጽሁፍ መዋቅሮችን በመገንዘብ ትምህርታዊ ክሂሎችን ለማዳበር እና ቋንቋን ለመማር በጣም ጠቃሚ መሆናቸው እና በአይነታቸው የተለያዩ በመሆናቸው በየተማሪዎቹ ደረጃ ተስማሚ ተረቶችን በመምረጥ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር መርዳታቸው ተረቶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ምቹ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም Bagous (2019) ተረቶችን መጠቀም እና ተረቶችን መሰረት ያደረጉ የመማር ተግባራትን በክፍል ውስጥ በሰፊው መተግበር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ጠቃሚ ነው በማለት ሀሳቡን ይደግፋሉ፡፡

በዚህ መሰረት መጻፍን መማሪያ እና ማስተማሪያን መምረጥ ሲታሰብ እነ Ellis (2014) Hutchinsm (1987) ን ጠቅሰው እንደገለጹት የማቴሪያሎቹ ሚና ሞዴል እና ማጣቀሻ መሆን፣ የቋንቋ ድጋፍ መስጠት ፣ገፋፊ መሆን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተረቶችን መጻፍን ለማስተማሪያነት መጠቀም ተማሪዎች ለመጻፍ እንዲገፋፉ ፣ሞዴሎችን እንዲያገኙ እና ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ ያግዛቸዋል፡፡

## ተረትን በመጠቀም መጻፍን ማስተማር

ተረትን በመጠቀም መጻፍን ማስተማር የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ለምሳሌ Rajathurol (2020) እንደሚገልጹት፣ የተረቶች የፈጣንነት እና የድግግሞሽ ባህሪ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን እና ሰዋሰውን መማር እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የመማር ሂደት ተረቶችን በመጠቀም ህጻናት መማር ሲጀምሩ መሳተፍ እንዲችሉ በማገዝ ካለምንም ችግር ትምህርቱን የመከታተል እና የመገንዘብ አቅም በማሳደግ ስነትምህርታዊ ስኬታማነትን በማስገኘት ረገድ በትምህርት ቤት ውስጥ በጣም ጠቃሚ ናቸው ፡፡

የቋንቋ መምህራን ስነጽሁፎችን (ተረቶችን) በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ምክንያቶች፡- ተጨባጭ ማቴሪያልነታቸው፣

ለማስተማሪያ ተብለው ለተለየ ዓላማ አለመዘጋጀታቸው፣ የቋንቋውን ተናጋሪ (አፊ ፊት) የቋንቋ አጠቃቀም ለማወቅ ማስቻላቸው፣ቋንቋዊ ብልጽግናቸው እና ግላዊ አካታችነታቸው መሆናቸውን Coille and Slater (1987) ይገልጻሉ፡፡

ተረቶችን በመጠቀም ማስተማር ታላሚውን የቋንቋ ክሂል ለማዳበር ይረዳል፡፡Fakhrutdinova (2009) እና Putri(2019) በጥናታቸው Swan(1985) ጠቅሰው እንደገለጹት ተማሪዎች ተረቶችን በመጠቀም በታላሚው ቋንቋ ይዘትን መሰረት ባደረገ ማስተማር ሲማሩ በሚያገኙት አውዳዊ እውቀት የቋንቋውን አጠቃቀም በቀላሉ በመረዳት የቋንቋውን አጠቃቀም በማወቅና ይዘቶችን በማግኘት ለመማር ስለሚረዳቸው የተፈለገውን ክሂል ለማዳበር ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በዓይነቱ መጠናዊ ሲሆን፣ ከፊል ፍትነታዊ (Quasi-Experimental) የምርምር ስልትን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑት መረጃዎች መጠናዊ በሆነ መንገድ ተተንትነው ተረትን በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር የሚኖረው ሚና በቅድመ ትምህርትና ድኅረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች ተለይቷል፡፡ የተደረሰበት ማጠቃለያና ይሁንታም ቀርቧል፡፡

### የአጠናን ሂደት

ይህን ጥናት ለማከናወን መጀመሪያ በጥናቱ የተመረጠውን ትምህርት ቤት ፈቃድ ለማግኘት ከጅማ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል የትብብር ደብዳቤ በማስጻፍ ጥናቱን ለማከናወን ለተመረጠው አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ ለክፍል ደረጃዋ የአማርኛ ቋንቋ መምህርት፣ ለሱፐር ቫይዘሯ እና በጥናቱ ለሚሳተፉት ተማሪዎች የጥናቱ ዓላማ ተገልጾላቸው ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በጥናትና ምርምሩ ተሳታፊ ከሆነችው መምህርት ጋር በመወያየት፣ ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን ስለማስተማር ዘዴ ምንነት፣ አተገባበር፣ ተማሪዎች ስለሚያከናውኗቸው የመማር ተግባራት እና ስለሚኖራቸው ሚና እንዲሁም ስለመምህርቷ ተግባር (የተማሪ እና የመምህር ተግባር እና ኃላፊነት) ግንዛቤ እንዲኖራት ለሁለት ቀናት የአራት ሰዓት ስልጠና ተሰጥቷታል፡፡በመመሪያው መሰረት የተዘጋጀ ማስታወሻም ተሰጥቷታል፡፡ በቀጣይ ቀናት በማስታወሻው ላይ ግልጽ ያለሆኑላትን ሀሳቦች እና

ጥያቄዎች በማብራራት እና በመወያየት ወደስራው እንድትገባ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡

ቀጥሎ የተገባው ተጠኚዎቹን የሙከራና የቁጥጥር ብሎ ለመመደብ ተመሳሳይ የመጻፍ ችሎታ ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን ለመለካት የሚያስችለውን ፈተና ወደ ማዘጋጀት ነው፡፡ ፈተናው ከመዘጋጀቱ አስቀድሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርት ሚኒስቴር በ2007 ዓ.ም የተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ እና የተማሪው መጻሐፍ አምስተኛ ክፍል፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርት ሚኒስተር በ2013 ዓ.ም ያዘጋጀው የአጠቃላይ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል) ይዘቶች፣ ፍሰት ቻርቶች፣ ተፈላጊ ብቃቶች እና መርሃ ትምህርቶች ተፈትሸዋል፡፡

የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናው ዓላማ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የነበሩበትን ደረጃ ለማወቅ በመሆኑ በመማሪያ መጽሐፉ መጻፍን ለማስተማር ከተዘጋጁት ጥያቄዎች ጋር በይዘትም ሆነ በቅርጽ ተቀራራቢነት ያላቸው ጥያቄዎች ተዘጋጅተውና በመምህራን ተገምግመው ተማሪዎቹ በተመሳሳይ ሰዓት እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት ስሌት ተሰርቷል፡፡ የቲ- ስሌት ዋጋው የጉልህነት ደረጃ ፆ P = 0.690 (P>0.05) በመሆኑ ወይም የተገኘው የቲ-ዋጋ ቲ(92)= 0.400 ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ (1.984) በማነሱ በተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን በማመልከቱ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖቹ በእጣ ተመድበዋል፡፡

ለሙከራ ቡድኖቹ ማስተማሪያ የሚሆኑ ተረቶችን የመምረጥ ሥራው ከዚህ ጎን ለጎን ተካሂዷል፡፡ መጻፍን ለማስተማር የተመረጡት ተረቶችም ከተለያዩ መጻህፍት የተመረጡ ሲሆኑ፣ ይህም የተደረገበት ምክንያት ለተማሪዎች ደረጃ የሚመጥኑ ተረቶችን ለማግኘት በማሰብ ነው፡፡
በአጥኝዋ ለደረጃው ይመጥናሉ ተብለው ከቀረቡት አስራ ሶስት አማራጭ ተረቶች በክፍል ደረጃው መምህራን እና በደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አስተያየት ተሰጥቶባቸው አስር ተረቶች (አንድ ቁራ እና አንድ ቀበሮ፣ጨው ተሸካሚው አህያ፣የአንድ አባት ኑዛዜ፣ የታማኝ ወዳጆች መከዳዳት፣ ኤሊ እና ሶስት ጓደኞቿ፣ ክፉ ቀን ፣ የንጉሱ የካህን ግራ ዐይን፣ ባለ እዳዋ ጥንቸል፣ ገበሬና ታማኝ ውሻው እና አንበሳ እና አይጥ) ተመርጠዋል፡፡ የተሰጡት አስተያየቶች ከጭብጥ፣ ከሥርዓተ ጾታዊ እና አካትቷዊ ጉዳዮች፣ ከቋንቋ

አጠቃቀማቸው እና ከአካባቢያዊነታቸው አንጻር ባላቸው ተገቢነት ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡

ቀጥሎ የተገባው ወደ ትምህርቱ ትግበራ ነው፡፡ ለቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው መሰረት፣ ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን የማስተማር ስራው ለአምስት ሳምንታት (10 ክፍለ ጊዜ) ትምህርቱ ቀርቧል፡፡ የሙከራ ቡድኑ የመጻፍ ትምህርትም ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን ስለመማር ዓላማ በግልጽ ከተብራራላቸው በኋላ፣ ሞዴል ሆኖ ሰርቶ ማሳየት፣ በጋራ በመስራት እና ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው እንዲሠሩ በማድረግ ቀስ በቀስ በራስ መጻፍ መቻልን እንዲተገብሩ ተደርጓል፡፡ በትግበራውም የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመከታተል በመምህሯ እለታዊ እቅድ መጨረሻ ላይ ግለ ጽብረቃ በማድረግ በየክፍለ ጊዜው የነበረውን ሁኔታ መዝግቦ በመገምገም ለቀጣይ ክፍለ ጊዜ ግብዓት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ለአምስት ሳምንታት ትምህርቱ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ከተሰጠ በኋላ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖቹ ድኅረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ መረጃ ፈተና ተዘጋጅቷል፡፡ የፈተና ጥያቄዎቹ፣ ተገቢ ቃላትን መርጦ አረፍተ ነገሮችን የሚሟላት፣ ጅምር አንቀጾችን በተገቢ ቃላት እና ሀረጋት የማሟላት፣ ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው የመጠቀም እና ርእስ በመስጠት አንቀጽ የመጻፍ ጥያቄዎችን ያካተቱ ናቸው፡፡ የጥያቄቹ ተገቢነት ከተረጋገጠ በኋላ፣ ሁለቱም ቡድኖች በተመሳሳይ ሰዓት እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ መጻፍን ከማስተማር መማር ክንውን በኋላ የቀረበው ድኅረ ትምህርት ፈተና ዓላማ ተረትን በመጠቀም መጻፍን በማስተማር እና በተለመደው መንገድ መጻፍን በማስተማር መካከል የተፈጠረውን ልዩነት ለመመርመር ማስቻል በመሆኑ ይህንኑ የሚያሳዩ መረጃዎች ተሰብስበውበታል፡፡

## የጥናቱ ተሳታፊዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተረቶችን በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ያለውን ሚና መመርመር ሲሆን ለጥናቱ የተመረጠው አካባቢ ደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ ካራጉቱ አንደኛ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ የጥናት አካባቢ የተመረጠው በአመች ናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው፡፡ ይህ የንሞና ዘዴው የተመረጠው አካባቢው የአጥኟዋ የስራ ቦታ በመሆኑ ለጥናቱ ዓላማ መሳካት አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ይቻላል ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡ በደሴ ከተማ ከሚገኙት 32 አንደኛ ደረጃ ሙሉ እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ የካራ ጉቱ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በአምስተኛ ክፍል

ከሚማሩት 246 ተማሪዎች መካከል በሁለት ክፍሎች የሚማሩ 94 (47 የሙከራና 47 የቁጥጥር ቡድን) ተማሪዎች በተራ እጣ የንሞና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡

### የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የጥናቱን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተማሪዎቹን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ክሂል ችሎታዎቻቸውን ሊለኩ የሚችሉ ፈተናዎች ናቸው፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተናው በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖቹ መካከል ከመነሻው ጉልህ የመጻፍ ችሎታ የሌላቸው መሆኑን ለመፈተሽ ረድቷል፡፡ የድኅረ ትምህርት ፈተናው በአንድ በኩል በሙከራና በቁጥጥር ቡድኖቹ መከካል የታየውን ልዩነት በሌላ በኩል በሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድኅረ ትምህርት የፈተና ውጤቶች ለማነጻጸርና ተረቶችን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የሚኖረውን ሚና ለመለየት አገልግሏል፡፡

### የመረጃ ማጣራትና አደረጃጀት

ከጥናቱ ተሳታፊዎች የፈተና ውጤቶች የተሰበሰቡት መረጃዎች ለትንታኔ ከመቅረባቸው አስቀድሞ የተሰጡት መልሶች በተጠየቃዊ መንገድ የተሞሉ ስለመሆናቸው የማጣራት ሥራ ተከናውኗል፡፡ መረጃው ለትንተና በሚያመች መልኩ ኮድ ተደርጎ፣ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (ኮድ ሽት) በኮምፒውተር ላይ እንዲሰፍር ተደርጎ ወደትንታኔ ከመገባቱ በፊት በተሞላው መረጃ ላይ ማጣራት ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹ በይዘታቸው በአግባቡ ተደራጅተው በ "spss version 25" ሶፍትዌር ገብተው በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

### የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የጥናቱን ተሳታፊዎች የመጻፍ ችሎታ ለማወቅ በቅድመ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበው መረጃ በባእድ ናሙና ቲቴስት (Independent Samples t-test) ተሰልቷል፡፡ በተረቶች መጻፍን ማስተማር በመጻፍ ችሎታ ላይ ልዩነት መፍጠር አለመፍጠሩን ለመፈተሽ በድኅረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበው መረጃ በተመሳሳይ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test) እና በጥንድ ናሙና ቲቴስት (Paired Samples T-test) ተሰልቷል፡፡

## የመረጃ ትንተና

በጥናቱ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የቅድመ እና የድኅረ ፈተና ውጤቶች መረጃዎች በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ የተገኘው ውጤትም ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ተገልጿል፡፡

**ሠንጠረዥ አንድ፣** የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖቹ ቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test)

| ቡድን | ናሙና (no.of samples) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (St,Dev) | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 47 | 39.8404 | 15.31875 | -.400 | 92 | .690 |
| የሙከራ | 47 | 41.1383 | 16.14160 | | | |

በሰንጠረዡ እንደሚታየው የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች ተቀራራቢ ሲሆን የመደበኛ ልይይቱም እንዲሁ ተቀራራቢ ነው፡፡ ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የሁለቱ ቡድኖች የመጻፍ ችሎታ ውጤት ከየአማካዩ ውጤቶቻቸው ያላቸው እርቀትም ተቀራራቢ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ከላይ በቀረበው ሀሳብ መነሻነት በሁለቱ ቡድኖች መካከል በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ከታወቀ በኋላ የሙከራ ቡድኑ ተረትን በመጠቀም፣ የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው መንገድ መጻፍን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ የተገኘው የድህረ የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ ሁለት፣** የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test)

| ቡድን | ናሙና (no.of samples) | አማካይ (Mean) | መደበኛ ልይይት (St,Dev) | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነት Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 47 | 39.9043 | 17.72453 | -4.686 | 92 | .000 |
| የሙከራ | 47 | 57.2766 | 18.21783 | | | |

በሰንጠረዥ ሁለት እንሚታየው የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናው ውጤት የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 57.277 ከቁጥጥር ቡድኑ 39.901 በ17.37 ያህል መብለጡን ያሳያል ፡፡ የመደበኛ

ልይይታቸውም ውጤት የሙከራ ቡድኑ 18.22፣ የቁጥጥር ቡድኑ 17.72 ሆኖ ታይቷል፡፡ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ውጤት በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት መሰረት (t= -4.69 ,df= 92 , p=.000) ሆኗል፡፡ ይህ የተገኘ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር በመጻፍ ክሂል ላይ መሻሻል ያሳየ መሆኑን ያመላክታል፡፡

ሰንጠረዥ ሦስት፡- የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ እና የድኅረ ትምህርት የመጻፍ ፈተና ውጤት ተናጥላዊ ንጽጽር በጥንድ ናሙና ቲ ቴስት ሲሰላ

| ቡድን | የፈተና አይነት | የጽህፈት ውጤት | | | ተቀንሶ የተገኘ የልዩነት አማካይ ነጥብ | ተቀንሶ የተገኘ የልዩነት መደበኛ ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የተሰላ የ P ዋጋ | የተሰላ የቲ ቴስት ዋጋ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | | | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | ቅድመ ትምህርት | 47 | 39.840 4 | 15.318755 | 0.639 | 2.40578 | 46 | .978 | -027 | የለም |
| | ድህረ ትምህርት | 47 | 39.943 | 17.7245 | | | | | | |
| ሙከራ | ቅድመ ትምህርት | 47 | 40.554 3 | 15.81006 | 16.3370 | 2.414414 | 46 | .000 | -6.717 | አለ |
| | ድህረ ትምህርት | 47 | 56.891 3 | 18.22450 | | | | | | |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት አማካይ 39.9043 ከቅድመ ትምህርቱ አማካይ ውጤት 39.8404 ጋር ሲነጻጸር በልጦ የታየው በ0.0639 ነው፡፡ ይህም ልዩነት ጉልህነት መኖርና አለመኖሩን በ46 የነጻነት ደረጃ፣ በጥንድ ናሙና ቲ- ቴስት ሲሰላም የቲ ዋጋ -.027 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው (P>0.05) 0.978 ሆኗል፡፡ ይህም በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ሰፊ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

የሙከራ ቡድኑ ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት አማካይ 56.8913 ከቅድመ ትምህርቱ አማካይ ውጤት 40.5543 ሲነጻጸር በልጦ የታየው በ16.3370 ነው፡፡ ይህ ግን ከላይ ከተመለከትነው ከቁጥጥር ቡድኑ ከፍተኛ ብልጫ ያሣየ ነው፡፡ ይህም ልዩነት ጉልህነት መኖርና አለመኖሩን በ46 የጉልህነት ደረጃ፣ በጥንድ ናሙና ቲ- ቴስት ሲሰላም የቲ ዋጋ -- 6.717 ሲሆን የጉልህነት ደረጃውP= .000 (P<0.05) ነው፡፡ በመሆኑም በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች መጻፍን በተረቶች በመማራቸው የመጻፍ ክሂላቸው መሻሻሉን ነው፡፡

እንደ አጠቃላይ የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ እና ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ከሙከራ ቡድኑ ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ያነሰ መሆኑን፣ የቁጥጥር ቡድኑ ውጤትም የተወሰነ መሻሻል እንዳሳየ

ነገር ግን መሻሻሉ ከሙከራ ቡድኑ ያነሰ እንደሆነ ከላይ ካለው ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡

## የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ መላምት ‹‹ተረትን በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል አያዳብርም፡፡›› የሚል ሲሆን በሰንጠረዥ አንድ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት መካከል ያለው መረጃ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲሰላ ውጤቱ t (92) = 0.400፣ p = 0.690 ሆኖ ታይቷል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የ (p) ዋጋ p>0.05 ከሚለው መነሻ በልጦ መገኘት Pallent (ጉልህ ልዩነት (significant difference) አለመኖሩን እና 2010) እና Greasley (2008) እንደሚገልጹት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ይህ ነው የሚባል ቡድኖቹ በተመሳሳይ ደረጃ ተገኝተዋል፡፡ ከድህረ ትምህርት በኋላ በተሰጠው ፈተና የተገኘው የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 39.90፣ መደበኛ ልይይት (Std.Deviation) 17.72 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 57.28 መደበኛ ልይይት (Std.Deviation) 18.22 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የታየው የአማካይ ውጤት ልዩነት 17.37 ነው፡፡ ይህ ውጤት የሙከራ ቡድኑ አማካይ ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት ከፍተኛ ብልጫ ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡

ይህ ውጤት ተረቶችን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች የመጽፍ ችሎታ ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ ካረጋገጡት የMantra (2019)፣ የPutri (2019) እና የNur (2017) ጥናቶች ጋር ተደጋጋፊ ሆኗል፡፡ በእነዚህ ጥናቶች የሙከራ ቡድኖቹ ተማሪዎች ውጤት ከቁጥጥር ቡድኖቹ ተማሪዎች ውጤት የተሻለ ልዩነት እንዳሳየው ሁሉ በዚህ ጥናትም ተመሳሳይ ውጤት ተገኝቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሰንጠረዥ ሁለት የቀረበው መረጃ የባእድ ናሙና ቲ-ቴስት እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ የድህረ ፈተና ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቅድመ ትምህርት ፈተናው የባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት t (92) = 0.400,P< 0.690 ሲሆን የ t ዋጋ በ t ሰንጠረዥ ከሚገኘው ዋጋ (1.984) ያነሰ በመሆኑ በተማሪዎቹ መካከል ልዩት የሌለ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በድህረ ፈተናው የተገኘው የባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤት ደግሞ t (92) = 4.686 ,P<.000 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በድህረ ፈተናው የተገኘው የ t (4.686) ዋጋ በ t ሰንጠረዥ ከሚገኘው (1.984) ዋጋ በ2.702 በልጦ ተገኝቷል፡፡ ብልጫው ሙከራ ቡድኑ ውጤት ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሠንጠረዥ ሁለት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖቹ ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ንጽጽር በባእድ ናሙና ቲቴስት (Independent Samples t-test) ተሰልቶ የቡድኖቹ ልዩነት በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲሰላ (t = -4.686፣ df = 92፣ p=.000) ሆኗል፡፡ ይህም የቡድኖቹ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተረትን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር የሚጠቅም መሆኑን ያመላክታል፡፡ እነዚህ ውጤቶች በBagous (2017)እና በ Fakhrutdinova፣2009)፣ ጥናቶች እንደተገለጸው፣ ተረቶችን መሰረት ያደረጉ የመማር ማስተማር ተግባራትን በክፍል ውስጥ መተግበር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ጠቃሚ መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተረቶቹ ተማሪዎቹ የባህሉ አካል ከሆኑበት ህዝብ ስለሚፈልቁ ለተማሪዎቹ እንግዳ ካለመሆናቸው እና ተጨባጭ ቃላትን ለመማር በሞዴልነት ከማገልገላቸው ጋር በተያያዘ በዚህ ጥናት እንደታየው እና በ(Prastiwi, p.2015) ጥናት እንደተመለከተው የመግቢያ፣ የዋና አካልና የመደምደሚያ ቅርጾቻቸው ተማሪዎቹ ይህንኑ መዋቅር ተከትለው እንዲጽፉ ከማገዛቸው የመጣ ውጤት ነው ቢባል ተጠየቃዊነት ይኖረዋል፡፡

ተረቶች በማንኛውም እድሜ ለሚገኙ ተማሪዎች ተስማሚዎች መሆናቸው በ(Lwin, 2009) ጥናት እንደታየው ተረቶች በክፍል ውስጥ በተማሪዎቹ የዕድሜ ልዩነት ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ማቃለል፣ በአውድም ሆነ ከአውድ ውጭ ትርጉም የመስጠት ባህርይ ያላቸው መሆኑ (Taylor, 2000) እና የመግቢያ፣ የመተንተኛና የማጠቃለያ መዋቅሮችን መያዛቸው፣ ተማሪዎቹ በዚሁ ቅርጽ ጽሑፎችን እንዲያዋቀሩ መነሻ ስለሆኗቸው የተመዘገበው ውጤት እንደተገኘ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

## ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሐሳብ

### ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተረቶችን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር በተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ ላይ ለውጥ የሚያመጣ መሆን አለመሆኑን መመርመር ነው፡፡ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በቀላል እጣ ናሙና የተመረጡ ሁለት የአምስተኛ ክፍሎች በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን ተመድበው ለአምስት ሳምንታት ያክል ትምህርቱ ሲሰጥ ቆይቶ የተገኘው የፈተና ውጤት ተረትን በመጠቀም የመጻፍ ክሂልን ማስተማር በተለመደው መንገድ የመጻፍ ክሂልን ከማስተማር በተሻለ የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ማስቻሉን አሳይቷል፡፡ ይህ ውጤትም ሥነ ጽሁፍ

ተማሪዎችን ከበርካታ ስነልሳናዊ ጠቀሜታዎች ማለትም ከሥነልሳናዊ አጠቃቀሞች፣ ቅርጾች እና የጽህፈት ሥርዓት ስምምነቶች፣ ከተለያዩ የጽሁፍ ቋንቋ ባህሪያት ጋር በማስተዋወቁ የመጣ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ተረትን በመጠቀም ማስተማር በተለመደው መንገድ ከማስተማር የተሻለ ውጤታማ እንደሆነ አሳይቷል፡፡

**የመፍትሄ ሀሳብ**

መጻፍ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ አጫጭር ጽሁፎችን የመጻፍ ችሎታቸውን ሊያበለጽጉ እና ሊያሳድጉ የሚገባቸው መረዳትን የሚጠይቅ አፍላቂ ክሂል መሆኑን ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ከክሂሉ ጠቀሜታ አንጻር ጥሩ የመጻፍ ችሎታን ለማሳደግ የማስተማር ሚና እንዲጎላ ትኩረት የተሰጠው መሆኑም ተገልጿል፡፡ በኢትዮጵያ የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት የመጻፍ ክሂልን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱም ተጠቅሷል፡፡

እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ቢኖሩም፣ በተመራማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ችግሮች መኖራቸውን ያሳያሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከተደረጉ ጥረቶች መካከል የመጻፍ ክሂልን በሥነ ጽሑፍ ማስተማር ተጠቃሽ ነው፡፡ በሌሎች ጥናቶች እንደተመዘገበውና በዚህ ጥናት ውጤትም እንደታየው፣ ተረቶችን ተጠቅሞ መጻፍን ማስተማር በተለመደው ዘዴ መጻፍን ከማስተማር የተሻለ ውጤት ያስገኛል፡፡

ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ተረትን በመጠቀም መጻፍን የማስተማር ዘዴን በክፍል ውስጥ ቢተገብሩ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳቸዋል፡፡ በዘዴው የማስተማሩን ሥራ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፣ ለመምህራኑ ዘዴውን የመጠቀም ሥልጠና በትምህርት ባለሙያዎች ቢሰጣቸው መልካም ይሆናልና የሚመለከታቸው አካላት ለዚህ ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩ መልካም ይሆናል፡፡

## Declarations

### Conflict of interst

We would like to confirm that this research is my own work and free from any Interest conflict.

### Acknowledgment

We acknowledge Jimma University for providing financial support to conduct research. Besides, we appreciate Karragutu primary school directors, supervisors, Amharic teacher Wor. Bezu, and grade 5 students for their cooperation in implementing the research.

## References

ዋቢዎች

ማረው አለሙ ። (1996) ። *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ* ። ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ተስፋዬ ሸዋዬ ። (1981) ። *ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር* ። አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ ። (ያልታተመ)

ነብዩ ጋሹ። (2005) ። *በግጥም አማካኝነት በአማርኛ አንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ችሎታንማዳበር*: አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ዘመንፈስ ባራኪ። (1991) ። *በስነጽሁፍ አማካኝነት የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና*: አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ (ያልታተመ)።

የአምላክሥራ ሕይወት። (2008) ። *የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጭ ትንተና*። አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ። (2007) ። *አማርኛ ቋንቋ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህር መምሪያ አምስተኛ ክፍል*። ንግድ ማተሚያ ድርጅት። አዲስ አበባ።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስተር ። (2013)። *የአጠቃላይ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ (1/ኛ-8ኛ ክፍል) ይዘቶች፣ፍሰት ቻርቶች፣ተፈላጊ ብቃቶችና መርሃ ትምህርቶች*። ባህርዳር።

ያለው እንዳወቀ። (2009) ። *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር* ። 3/ኛ እትም። ተፈራ ስዩም ማተሚያ ቤት:ባህርዳር።

ግዛቸው አግማሴ። (2014) *። ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ* ። ጅማ ዩንቨርሲቲ (ያልታተመ)።

AL-Zoubi, S. M., & AL-Ghazo, A. (2018). *How to Develop Writing Skill through Constructivist Design Model. International Journal of Business and Social Science, 9*(5), 91-97: https://doi:doi:10.30845/ijbss.

Aray, D., Jacobs, L .C, Sorensen, C.K., & Razalieh, A. (2006). *Introduction to Research In Education Language Learning.* 8th ed. https:// www ebookppsunp.wordpress.com/wp

Beshir Elbashir. (2023). Writing Skills Problem, Causes and Solutions. *International Journal of English Language Teaching, 11*(5), 53-64: https://doi.org/037745/

Broughtan, G., Brumfit, C., Flavell, R., Hill, P., & Pincas, A. (1980) .*Teaching English as a Foreign Language.* (2nd.ed.) https://doi.org/10.4324/9780203412541

Brown, H. D. (2000). *Teaching by Principles an Interactive Approach to Language Pedagogy*. (2nd .ed.) https://octovany.wordpress.com/wp-

Cole, J. & Feng, J. (2015) .*Effective Strategies for Improving Writing Skills of Elementary English Language Learners.* Chinese American Educational Research and Development Association Annual Conference April 15-16, 2015 in Chicago, ILhttps://www.scribd.com/

Dakowska, M. (2018). *Teaching English as a Foreign Language: A Guide for Professionals.* https://www.researchgate.net/

Darmayanti, D., Hartati, H., Muslimin, F.F. & Khafimah, N. (2024). Improving Students' Writing Skill in Teaching Narrative Text by Using Indonesian Folktales. *Jurnal Ilmu Pendidikan,6*(1), 594-603: https://doi፡1031004/edukativ.v6i1.625

Ellis, G. & Breuster, J. (2014). *The Story Telling Handbook for Primary School Teachers.* (2nd ed.). https://www teachingenglish.org.uk

Fakhrutdinova, A. V.(a) ,Chumarova ,L. G.(b), Bellaeva ,E. A.(c), & Sagitova ,R S. (d) (2019). *Pedagogical Value of Folklore Prosaic Genres in Intellectual and Moral Education of Future Teacher's at the Foreign Language Lessons*. (121-125). https://dx.doi:10.3897/ap.1.e0111

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education. (2019) *Curriculum Framework for Ethiopian Education. (KG-Grade 12).* https://moe.gov.et/

*Guidance on Teaching Writing Skills.* (2009/2010).https://dera.ioe.ac.uk/

Hall, G. (2005). *Literature in Language education*. Research and Practice in Applied Linguistics serious. https://www.academia.edu/

Hill, J. (1986). *Using Literature in Language Teaching*. Macmillan. Publishers Ltd

Kantor, P. T. (2012). *Development of Writing: Key Components of written Language*. http://dx.doi.org:10.1007/s11145-010-9266-7

Langan, J. (2008). *Writing Skills with Readings*. (7th ed.). https://blaw05.wordpress.com/

Lazar, G. (1993). *Literature and Language Teaching: A guide for Teachers And Trainers*. https://www.academia.edu/

Lwin, S. M. 2015. *Using Folktales for Language Teaching.* XLIV, (2), 74-83: htpps://www.melta.org.my /TET/

Mantra, I .B.N. (2017). Promoting Students Writing Skill through Folktale Based Learning Activities. *International Seminar on Language, Education,& Culture*. https://www.researchgate.net /

Mckay, S. (1986). *Literature in Language Classroom.* in Brumfit, C.J. and R.A.Carter (Eds.).Literature And Teaching. Hong Kong: Educational Law- priced Book Scheme with Oxford University Press.

Mustefa, E. (2016). *Literature in English Language Teaching*. *European Journal of Language and Literature*. Doi:10.26417/ejis.v4/1.p157-162

Nodoushan, M.A. (2014). *Assessing Writing: A Review of the Main Trends*. Iranian Institute for Encyclopaedia Research. *1*(2,) 119-129: https:// files. eric. ed.gov

Nunnan, D. (1991). *Language Teaching Methodology: A textbook for teachers.* https://www.academia.edu/

Nur, H. (2017). Improving Students Writing Skill in Teaching Narrative Text by using Indonesian Folktales. *Didaktika Jurnal Kependidikan.1*(1), 95-111.

Pallent, J. (2010). *SPSS survival Manual: A Step by Step Guide To Data Analysis Using SPSS Program*. (4th ed. ) https://vle.upm.edu.ph/

Prastiwi, Y. (2015*). Folktales as a Medium of Teaching English: two primary Schools in Solo.* https://dro.deakin.edu.au/

Putri, A. S. (2019). *Using Folktales to Teach Writing Skill at the Eight Grade Students of SMPN/TANETE.* https://index.salnesia.id/

Richadrs, J. (2001). *Approaches and methods in language teaching* 2nd ed. https:// Victor Anglo. files. word press.com.

Rietdijk, S., Weijen, D .V. & Bergh, H. V. d. (2017). Improving writing in Primary Schools through a Comprehensive Program**.** *Journal of Writing Research*, *9*(2), 173-225: https://doi.org/10.17239/r

Shunk, D. H. 2012. *Learning Theories an Education Perspective*. (6th ed.) :https://spada.uns.ac.id/

Spark, R. (1985). *Literature, Reading, Writing and ESL. Bridging the Gaps*.*TESOL*, *19(*4) 703-725: https://doi : 10.2037/3586672

Widdowson, H. G. (1982). *The use of literature*. *On TESOL'81*, 203-214.

Yakoob, S. B. (2015). *Factors Affecting Student's Writing Skills in Primary Schools.* https://www.academia.edu/20824278/